https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year N.6
ADDIS ABABA 31st January, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፹፯/፪ሺ፲፬

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ዓላማና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.............................................ገጽ ፳፫ሺ፱፻

## Content

Regulation No. 487/2022

The Definition of Objectives and Function of the Ethiopian Investment Holdings Council of Ministers Regulation ……....................Page 23900

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፯/፪ሺ፲፬**

**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ዓላማና ተግባርን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ የተቋቋመ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ አደረጃጀትና ተግባር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት እንደሚወሰን በአዋጁ የተደነገገ በመሆኑ አደረጃጀቱንና ተግባራቱን ለመደንገግ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ስትራቴጂካዊ ፍላጎቶች ለማሟላት በሚያግዝ አኳኋን የግል ኢንቨስትመንት ከመንግስት ጋር በጋራ ልማት ስራዎች ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የግል ኢንቨስትመንትን በተጠናከረ ሁኔታ ለመሳብ የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 487/2022**

**THE DEFINITION OF OBJECTIVES AND FUNCTION OF THE ETHIOPIAN INVESTMENT HOLDINGS COUNCIL OF MINISTERS REGULATION**

WHEREAS, the Ethiopian Investment Holdings has been established under the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/2021;

WHEREAS, it is provided by the Proclamation that the organization and function of the Ethiopian Investment Holdings shall be defined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers and thereby it has become necessary to issue a Regulation that defines its organization and functions;

WHEREAS, there is a need to create an institutional framework that allows attraction of private investment into Ethiopia in a strengthened manner and creation of an enabling environment for enhanced joint investment between the private and public sectors in such a way that serves the strategic needs of the economy;

https://chilot.me



የተቀናጀ ስትራቴጂያዊ ቁጥጥር በማከናወን በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ ሪል-ስቴት፣ መሬት፣ መሠረተ-ልማቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የመሳሰሉት ሀብቶችን የተሟላና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ የሚቻልበትን ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግስት የሆኑ ሀብቶችን እና የሀብት ምንጮችን በማስተዳደር ረገድ ተገቢውን የገበያ ሥርዓትን በመከተል፣ በጠንካራ የኩባንያ መልካም አስተዳደር መርሆዎች የሚመሩ እንዲሆኑ ለማስቻል፤

ባለቤትነታቸው የፌደራል መንግስት የሆኑ የተለያዩ ሃብቶችን በአንድ ሕጋዊ ተቋም ስር እንዲተዳደሩ በማድረግ መንግስት ተገቢውን እና ዉጤታማ አመራር እንዲሰጥ ማስቻል እንዲሁም ከፍ ያለ የውጪ ኢንቨስትመንት እና ቴክኖሎጂ መሳብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፻፫ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ዓላማና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፯/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ **"መንግስት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ነው፤

፪/ **"የመንግስት ሀብት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛው የአክሲዮን ድርሻው በፌደራል መንግስት ባለቤትነት የተያዘ የመንግስት የልማት ድርጅት፣ የአክሲዮን ማሕበር ወይም የመንግስት የፋይናንስ

WHEREAS, it has become necessary to create an institutional framework that allows the full optimization of the value of the range of state-owned assets such as real estate, land, infrastructure and state-owned enterprises through a coordinated strategic oversight;

WHEREAS, it is imperative to uphold and incorporate strong corporate governance principles to instill commercial and investment discipline in the management of state-owned assets and resources;

WHEREAS, it has become necessary to bring together various state-owned assets under one legal entity, in a manner that allows the government to provide a strategic oversight, attract sizeable foreign investment and technology;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 103 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1263/ 2021, the Council of Ministers has issued this Regulation.

## SECTION ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "The Definition of Objectives and Function of the Ethiopian Investment Holdings Council of Ministers Regulation No 487/2022".

### 2. Definition

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1) "Government" means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2) "State-owned Asset" means a wholly or majority state-owned enterprise, share company or financial institution; land or building under state ownership or possession; and other tangible or intangible assets over which the Federal

https://chilot.me



ድርጅት፤ በመንግስት ባለቤትነት ወይም ይዞታ ስር ያለ መሬት ወይም ሕንፃ፤ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለ ግዙፍነት ያለው ወይም ግዙፍነት የሌለው ሃብት ነው፤

፫/ **“ቦርድ”** ማለት በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲ መሠረት የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤

፬/ **“ንዑስ ፈንድ”** ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በራሱ ወይም ከሌላ ንዑስ ፈንድ፣ የፋይናንስ ተቋም፣ ኩባንያ ወይም የመንግስት ተቋም ጋር በመሆን የሚያቋቁማቸው ፈንዶች ናቸው፤

፭/ **“ተቀጥላ”** ማለት ንብረትነቱ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሆነ ወይም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ባለአክሲዮን የሆነበት እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቁጥጥር ሚና ያለበት ድርጅት ወይም ኩባንያ ነው፤

፮/ **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰው ነው።

፫. <u>**መሰረቱ**</u>

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እንደ አስፈላጊነቱ በአጭር ስም “ኢ.ኢ.ሆ” በመባል ሊጠራ ይችላል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

፫/ መንግስት በባለቤትነት የያዘው የአክሲዮን ድርሻ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚያቋቁማቸው ወይም በባለድርሻነት የሚሳተፍባቸው ንዑስ ፈንዶች ወይም ኩባንያዎች እንደ የግል ንግድ ድርጅት ይቆጠራሉ፡፡

፬/ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፶፬ እንዲሁም በዚህ ደንብ በተለየ ሁኔታ ከተደነገገው በስተቀር የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ፣ የንግድ ሕግ እና ሌሎች

Government has full or partial ownership or other stake;

3) “Board” means the Board of Directors of the Ethiopian Investment Holdings established in accordance with Article 10 of this Regulation;

4) “Sub-Funds” means funds founded by Ethiopian Investment Holdings individually or holding or owning shares in them with counterpart funds, financial institutions, companies or any other public entity;

5) “Subsidiary” means company owned by Ethiopian Investment Holdings individually, or company in which Ethiopian Investments Holdings is a shareholder with other parties and maintains direct or indirect control;

6) “Person” means any natural or legal person

3. <u>**Basis**</u>

1) Ethiopian Investment Holdings may be referred by its short name “EIH” as necessary.

2) Ethiopian Investment Holdings shall be accountable to the Office of the Prime Minister.

3) Ethiopian Investment Holdings, as well as sub-funds and companies set up by Ethiopian Investment Holdings or it participates in setting up thereof shall be considered private business organization regardless of the shareholding percentage of the government.

4) Unless otherwise provided by Article 54 of the Definition of Powers and Duties of the Federal Executive Organs Proclamation No. 1263/ 2021 and this Regulation, the provisions of the Ethiopian Civil Code, the Commercial Code, and any other relevant laws shall

https://chilot.me



አግባብነት ያላቸው ሕጎች በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና በተቀጥላ ኩባንያዎቹ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱም ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች በሃገር ውስጥ ወይም በሌላ ሃገር ሊከፍት ይችላል።

## ፭. ዓላማ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ የኢትዮጵያ መንግስት ስትራቴጂያዊ የኢንቨስትመንት ተቋም ሆኖ የማገልገል፤

፪/ ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ያገኙ የኩባንያ መልካም አስተዳደር መርሆዎችን በመከተል እና በመተግበር እንዲሁም ብቃት ያለው አስተዳደርን ተግባራዊ ባደረገ መልኩ የመንግስትን ሀብት በማስተዳደር፤ አሁን ላለው እና ለመጪው ትውልድ ያለውን ዋጋ ማሳደግ እና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅኦ ለማበርከት በሚያስችል መንገድ ከሀብቱ ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት፤

፫/ የጥምር ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ መደላድልን በመፍጠር፣ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ሐብትን በማቀናጀት እንዲሁም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሀብቶች ላይ እሴት በመፍጠር የውጪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንደ ስትራቴጂያዊ መሳሪያ ሆኖ ማገልገል።

## ፮. ካፒታል

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የተፈቀደ ካፒታል ብር አንድ መቶ ቢሊየን ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር ሃያ አምስት ቢሊየን በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፪/ ቦርዱ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የተፈቀደ ካፒታል ሊያሳድግ፣ ሊቀንስ ወይም ወደሌላ ቅርጽ ሊለውጥ ይችላል።

apply to Ethiopian Investment Holdings and its subsidiaries.

## 4. Head Office

Ethiopian Investment Holdings shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices inside or outside Ethiopia.

## 5. Objective

The objectives of Ethiopian Investment Holdings are to:

1) Serve as a strategic investment arm of the government of Ethiopia;

2) Contribute to sustainable economic development, through professional management of its funds and assets achieving the optimal use thereof in accordance with international best practice and corporate governance principles, and to maximize the value for the benefit of current and future generations;

3) Provide a strategic vehicle to attract foreign investment by, among others, establishing a co-investment platform, consolidating assets for further monetization, unlocking values from current unutilized assets and thereby bring the highest possible return on investment.

## 6. Capital

1) The authorized capital of Ethiopian Investment Holdings is Birr One Hundred Billion of which Birr Twenty-Five Billion is paid up in cash and in kind.

2) The Board may increase, reduce or alter in any form the authorized capital of the Ethiopian Investment Holdings as provided under Sub-Article (1) of this Article.

https://chilot.me



## ፯. የገንዘብ ምንጭ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የገንዘብ ምንጭ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እንዲያስተዳድራቸው የተደረጉ የተለያዩ የመንግስት ሀብቶች፤

፪/ ከሀብቶቹ የሚገኝ ገቢና የኢንቨስትመንት ትርፍ፤

፫/ ከሀብቶቹ ወይም ከተቋማቱ ሽያጭ የሚገኝ ገቢ፤

፬/ ከቦንድ እና ከሌሎች የፋይናንስ ሰነዶች ሽያጭ የሚገኝ ገቢን ጨምሮ ከብድር እና ኤኢሆ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚገኝ ገቢ፤

፭/ በዳይሬክተሮች ቦርድ ፀድቆ የሚመደብ ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገቢ።

## ፰. ስለሃብት ማስተላለፍ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚያቀርበው የሀብት ማስተላለፍ ጥያቄ በዳይሬክተሮች ቦርድ ሲፀድቅ በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም ሌላ የመንግስት ሀብት ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ወይም በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ለተቋቋሙ እና ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ባለቤትነት ለተያዙ ንዑስ ፈንዶች እንዲተላለፍ ይደረጋል።

## ፱. ተግባር እና ኃላፊነት

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ) በኢትዮጵያ የንግድ ህግ ለሆልዲንግ ኩባንያ የተሰጠውን ተግባር ያከናውናል፤

ለ) ባለቤት የሆነባቸውን አክሲዮኖችን ፤የዕዳ ሰነዶችን፣ ቦንዶችን፣ የዋስትና ሰነዶችን ይይዛል፤

## 7. Source of Funds

The source of funds of Ethiopian Investment Holdings are the following:

1/ Pool of state-owned assets Ethiopian Investment Holdings administers as provided under this Regulation;

2/ Returns and revenues of the investment of its assets;

3/ Proceeds from the sale of its assets or entities;

4/ Loans and other facilities including proceeds of the issuance of bonds and other financial instruments;

5/ Other resources allocated to it and approved by the Board of Directors.

## 8. Transfer of Assets

Up on the Request of the CEO of Ethiopian Investment Holdings and with approval of the Board of Directors, the ownership of a state-owned enterprise or any other state-owned asset shall be transferred to the Ethiopian Investment Holdings or any of the funds established and fully owned by the Ethiopian Investment Holdings.

## 9. Duties and Responsibilities

1/ Ethiopian Investment Holdings shall have the following duty and responsibility:

a) Operate and carry on a business of a holding company as per the Ethiopian Commercial Code;

b) Hold shares, debentures, bonds and securities, which are in its ownership;

https://chilot.me



ሐ) አትራፊ ናቸው ብሎ በሚያምንባቸው ማንኛቸውም የንግድና የኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ ያፈሳል፣

መ) የካፒታል ገበያ፤ የገንዘብ ገበያ እና ሌሎች መሰል ዘርፎች ላይ በግዥ፤ በሽያጭ ወይም በሌላ የኢንቨስትመንት ተግባር ይሳተፋል፣

ሠ) በዚህ ደንብ አንቀፅ ፰ መሰረት በቦርዱ የሚመደብለትን የመንግስት ሀብት ተረክቦ ያስተዳድራል፤

ረ) የሚተላለፉለትን የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሌሎች የመንግስት ሀብቶች አደረጃጀት እና አሰራርን በመቀየር እና አዋጭ በሆነ መልኩ ስራ ላይ በማዋል ውጤታማና ትርፍ የሚያመነጩ አድርጎ ይለውጣል፤

ሰ) ንዑስ ፈንዶችን ያቋቁማል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣ ይመራል፣

ሸ) በተቋቋመ ድርጅት ውስጥ ብቻውን ወይም ከአገር ውስጥ ወይም ከውጪ አገር ባለሀብቶች ጋር በመሆን በጋራ አክሲዮኖችን ይይዛል፤

ቀ) የአንድን ኩባንያ ሀብት እና እዳ በሙሉ ወይም በከፊል ለመረከብ አዲስ ኩባንያ ወይም ኩባንያዎች ያቋቁማል ወይም ያደራጃል፤

በ) በስሩ ያሉ ተቀጥላ ድርጅቶችን ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣ ይመራል፣

ተ) የገበያ መርህን እና የዓለምአቀፍ ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ አስፈላጊ ሰራተኞች ይቀጥራል፤ ክፍያ እና ማበረታቻዎቻቸውንም ይወስናል፤

ቸ) በየትኛውም የዓለም ክፍል በስሩ ተቀጥላ ድርጅቶች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ይወስናል፤

ኀ) በስሩ የሚገኙ ተቀጥላ ድርጅቶችን መፍረስ፣ ውህደት፣ ክፍፍል፣ ሽያጭ፣ ወደግል ሀብት መዘዋወር ወይም ራሳቸውን ችለው መውጣት በሚመለከት የቅድመዝግጅት ስራ ያከናውናል፤ ይወስናል፣

c) Invest in any business and investment opportunities as it sees profitable;

d) Take part in capital market, money market and similar other sectors through purchase, sell or other investment undertakings;

e) Takeover and manage state-owned assets that may be assigned to it by the Board of Directors in accordance with Article 8 of this Regulation;

f) Transform property of state-owned enterprises and other assets transferred to it into optimal income generating ventures, through structure and system change;

g) Establish, control, manage and administer sub-funds;

h) Acquire share in existing entities or funds solely or in association with local or foreign entities;

i) Establish or promote a new company or companies for the purpose of acquiring or undertaking all or any of the assets and liabilities of said company;

j) Manage, supervise and exercise control of the subsidiaries under its pool;

k) Hire appropriate staff, determine their payment and incentives in accordance with commercial principles and international best practice;

l) Decide on matters of incorporation of any of its subsidiaries in any part of the world;

m) Undertake all preparatory works and decide on the dissolution, amalgamation, division, sale, privatization, spin-off of subsidiaries it calls into its pool;

https://chilot.me



ነ) የሚያቋቁማቸውን ወይም በስሩ የሚያስገባቸውን ድርጅቶች ሕጋዊ ቅርጽ ይወስናል፤

ኘ) ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር ምንጮች ይበደራል፣ ገንዘብ ያሰባስባል፣ የእዳ ሰነዶችን ያወጣል፣ ዋስትና ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ማንኛውንም እዳ ወይም ግዴታ ይሰርዛል፤

አ) እንደአግባብነቱ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለተቀጥላዎቹ መያዣ ወይም ዋስትና ይሰጣል፤

ከ) ተቀጥላቹ ከውጪ ወይም ከሃገር ውስጥ የገንዘብ አበዳሪዎች ወይም የንግድ ሸሪኮች እንዲበደሩ ወይም ለብድሮች ዋስትና እንዲሰጡ ስልጣን ይሰጣል፤

ኸ) ዓላማውን በሚፈፅምበት ወይም ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ከአገር ውስጥ ወይም ከውጪ አገር ፈንዶች ወይም ገንዘብ አበዳሪዎች ጋር ሊተባበር ወይም በስራ እንቅስቃሴያቸው ሊሳተፍ ይችላል፤

ወ) ቋሚ እና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ይከራያል፣ ያከራያል፣ ይጠቀማል፣ ይገለገላል፤

ዐ) እንቅስቅሴው ከሃገራዊ ኢንቨስትመንት፤ የእዳ ክፍያ፤ በጀት እና ሌሎች የፖሊሲ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ከገንዘብ ሚኒስትር እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ተቋማት አስፈላጊውን መረጃ እና ግብዐት ይወስዳል፣ ምክክር ያደርጋል፤

ዘ) ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ስራዎችን ይሰራል።

፪/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በባለቤትነት የያዛቸውን ተቀጥላ ኩባንያዎች በሚመለከት የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

ሀ) በኢትዮጵያ የንግድ ህግ የሆልዲንግ ኩባንያ ያለው ስልጣን ይኖረዋል፤

n) Decide on the company form of the entities it calls into its pool or decides to establish;

o) Borrow, raise money from local and foreign sources, issue debt instruments and secure or discharge any debt or obligations in such manner as may be considered fit;

p) Enter into any guarantee, indemnity or suretyship and to charge some or all of the subsidiaries for their respective debts as appropriate;

q) Authorize borrowing of funds or any other forms of indebtedness or guarantorship by its subsidiaries involving domestic and foreign financiers or business partners;

r) In carrying out its objectives, it may cooperate and participate with domestic and foreign counterpart funds and financial institutions;

s) Purchase, sell, rent, lease, exploit and utilize fixed and movable assets;

t) solicit input, data and have consultations with the Ministry of Finance and other relevant institutions to enhance the alignment of its activities with national investment, debt servicing, budgetary and other policy objectives;

u) Perform other activities necessary for the attainment of its objectives.

2/ With respect to subsidiary companies under its ownership; Ethiopian Investment Holdings shall have the duty and responsibility to:

a) Serve and fulfil the powers and functions of a holding company as per the Ethiopian Commercial Code;

https://chilot.me



ለ) በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ዘመናዊ የኩባንያ አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጉ ያደርጋል ፣ ዓላማቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን ተገቢ መመሪያዎች ያወጣል፤ መመሪያዎቹ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

ሐ) የካፒታል እድገት ወይም ቅነሳ፣ ሽያጭ፣ ጥምረት፣ ክፍፍል፣ ምስረታ፣ የመዋቅር ለውጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተቀጥላ ኩባንያዎችን የማዋሃድ ወይም እንደአዲስ የማቋቋም ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

መ) ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ ስትራቴጂ እና ዓመታዊ ዕቅድ መንደፋቸውን ይቆጣጠራል፣ ያፀድቃል እንዲሁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

ሠ) የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ ይቀርፃል፤ ያስፈጽማል፣

ረ) የማኔጅመንት ቦርድ አባላትን ይሾማል፣ ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይወስናል፤

ሰ) ግልፅ የአሰራር ሥርዓቶችን እንዲከተሉ ያግዛል፣ ጊዜውን የጠበቀ እና አግባብነት ያለው የፋይናንስ እና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ሊያቀርቡ የሚችሉበትን ሥርዓት ይቀርፃል፤ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

ሸ) ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ አደረጃጀት

### ፲. አደረጃጀት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፦

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ፤

b) Establish a system to enable them play appropriate role in the economy, enable them to develop modern corporate management, design proper guidelines that help them achieve their goals, and follow up the implementation of the same;

c) Decide on their increase or reduction of capital, sale, amalgamation, division, spin-off, or any other restructuring, either by taking over one or more subsidiary companies or by the formation of a new company;

d) Supervise that they have developed strategic and annual plan consistent with Ethiopian Investment Holdings' strategic plans, approve such plans and monitor implementation of the same;

e) Devise dividend policy, and cause to execute;

f) Appoint members of the management board and decide on their remuneration and other benefits ;

g) Assist them to follow transparent procedures; develop a system under which they issue timely and proper financial and performance reports; follow up implementation of same;

h) Perform any other task that is necessary for the attainment of its objectives.

## SECTION TWO
## ORGANIZATION OF THE ETHIOPIAN INVESTMENT HOLDINGS

### 10. Organization

Ethiopian Investment Holdings shall have the following governance structure:

1/ A Board of Directors;

https://chilot.me


፪/ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና የሥራ አመራር አባላት፤

፫/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤ እና

፬/ እንደአስፈላጊነቱ ገለልተኛ የሆነ ዓለምአቀፍ አማካሪ ቦርድ።

## ፲፩. የዳይሬክተሮች ቦርድ

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የዳይሬክተሮች ቦርድ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሰብሳቢነት የሚመራ ይሆናል።

፪/ በሰብሳቢው የሚሾሙ ስድስት (፮) አባላት የሚኖሩት ሲሆን የአገልግሎት ዘመናቸው በየሶስት ዓመቱ ሊታደስ ይችላል።

፫/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ድምፅ የመስጠት መብት ባይኖረውም ቦርዱ በሚያካሂዳቸው ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል።

፬/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ ሲሆን ሰብሳቢው ከጠየቀ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፭/ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ የሚወሰን ሲሆን እኩል ድምፅ በሚኖርበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው የውሳኔ ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፲፪. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣን እና ኃላፊነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተለው ስልጣን እና ኃላፊነት ይኖረዋል፦

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና የተቀጥላ ኩባንያዎቹ ንግድ የሚመራበትን ስትራቴጂ እና ራዕይ ይቀርፃል፤

፪/ ቦርዱ በሚያስቀምጣቸው የአፈፃፀም መለኪያዎች መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ስራውን እያከናወነ መሆኑን ይከታተላል፤

፫/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የስራ አመራር አባላት ሹመት፣ ስንብት፣ የካሳ ክፍያን ጨምሮ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሥራ አመራር መዋቅርን ያጸድቃል፤

2/ A Chief Executive Officer and Executive Management;

3/ Necessary staff; and

4/ An Independent International Advisory Board, as necessary.

## 11. Board of Directors

1/ The Board of Directors of Ethiopian Investment Holdings shall be chaired by the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

2/ The Board shall constitute 6 (six) members to be appointed by the chairperson for a term of three years which may be renewed.

3/ The CEO of Ethiopian Investment Holdings shall participate in the Board's meetings on ex-officio non-voting capacity.

4/ The Board shall meet once every month; provided however that it shall meet at any time at the request of the chairperson.

5/ Decisions of the Board shall be passed by majority votes and, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

## 12. Powers and Responsibilities of the Board of Directors

The Board shall have the power and responsibility to:

1/ Set the strategic vision and business direction of the Ethiopian Investment Holdings and its subsidiaries;

2/ Follow up the general performance of the Ethiopian Investment Holdings in accordance with the performance indicators developed by it;

3/ Approve the overall management structure of the Ethiopian Investment Holdings, including the assignment, compensation, and dismissal of members of the Executive Management of Ethiopian Investment Holdings;

https://chilot.me


፬/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና ሥራ አስፈፃሚን፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን እና የኦዲተርን ሹመት፣ ስንብት፣ ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይወስናል፤

4/ Determine the assignment, dismissing remuneration and other benefits of the CEO, senior management and Auditors of Ethiopian Investment Holdings;

፭/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን አጠቃላይ ፓሊሲ እና የውስጥ ደንቦች ይወስናል፤

5/ Adopt the general policies and internal regulations of Ethiopian Investment Holdings;

፮/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና ተቀጥላዎቹን መፍረስ፣ ከሌላ ጋር መዋሃድ፣ መከፋፈል፣ወይም ንብረትነታቸውን ወይም አስተዳደራቸውን በማናቸውም ሁኔታ ወደሌላ ተቋም መተላለፍን ያፀድቃል፤

6/ Approve the dissolution, amalgamation or division of Ethiopian Investment Holdings and its subsidiaries or the transfer of the ownership and supervision of Ethiopian Investment Holdings' subsidiaries to another authority in any other manner;

፯/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የተፈቀደ ካፒታል ያሳድጋል፣ ይቀንሳል ወይም ወደሌላ ቅርጽ ይለውጣል፤

7/ Increase, reduce, or in any form alter the authorized capital of Ethiopian Investment Holdings;

፰/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ተቀጥላዎች የአክሲዮን ድርሻ ወይም በአክሲዮን ድርሻ ላይ ያለውን ጥቅም መሸጥ፣ በመያዣነት ማስያዝ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገኖች ማስተላለፍን ይወስናል፤

8/ Decide on the transfer, pledge, mortgage or otherwise dispose of any share or any interest in any share of the subsidiary of Ethiopian Investment Holdings to third parties;

፱/ የአሰራር መመሪያዎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ዓመታዊ እቅዶችን፣ ግቦችንና በጀት ይወስናል፤

9/ Adopt the internal policies, operational guidelines, standards, budget, annual plans and targets of Ethiopian Investment Holdings;

፲/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የአስተዳደር፣ የፋይናንስ፣ እና የቴክኒክ ደንቦችን ይቀርፃል፣ የሰው ኃይል፣ የውል እና የግዢ ፖሊሲዎችን ይወስናል፤

10/ Develop the financial, administrative and technical regulations of Ethiopian Investment Holdings, personnel, contracts and procurement policies;

፲፩/ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ፓሊሲ እና መመሪያዎች መሠረት ዓመታዊ በጀትን ይወስናል፤ የአፈፃፀም ዓላማዎችን ያፀድቃል፤

11/ Determine and approve annual budgets and performance objectives in line with Ethiopian Investment Holdings policies and standards;

፲፪/ የኢንቨስትመንት፣ የአስተዳደር፣ የውስጥ ኦዲት፣ የስጋት አስተዳደር እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ጉዳዮችን የሚከታተሉ ንዑስ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤

12/ Form sub-committees to oversee investment, governance, internal audit, risks and other issues as necessary;

፲፫/ በዋና ሥራ አስፈፃሚ በሚቀርበው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የኢንቨስትመንት አቅድ ላይ ይወያያል፣ ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

13/ Discuss on investment plan of the Ethiopian Investment Holdings proposed by the CEO; approve and monitor the implementation of same;

https://chilot.me


፲፬/ ለሃገራዊ ኢንቨስትመንት፣ የእዳ ክፍያ፣ ለበጀት እና ሌሎች የፖሊሲ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስፈልገውን ሀብት ጨምሮ ቀጣይነት ያለውን ትርፍ ለመንግስት ማስገኘትን እና ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የወደፊት ኢንቨስትመንት የሚሆን ተቀማጭ ገንዘብ መያዝን ባመጣጠነ መልኩ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን እና ተቀጥላዎቹን የትርፍ አከፋፈል ፖሊሲ ይወስናል፤

፲፭/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ያፀድቃል፤ በኦዲት ሪፖርቱ መሠረት የተሰጡ የማስተካከያ እርምጃዎች መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

፲፮/ እንደአስፈላጊነቱ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የመተዳደሪያ ድንብ ያፀድቃል፤

፲፯/ የቦርድ አባላትን ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይወስናል፤

፲፰/ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የውስጥ ደንብ እና መመሪያ የተጠቀሱ ሌሎች ተግባራትን የመፈፀም እና መንግስት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና በተቀጥላዎቹ ውስጥ ያለውን የባለቤትነት ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ይፈፅማል፤

፲፱/ ቦርዱ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲፈፅም ለማንኛውም ሌላ ሰው፣ ኮሚቴ ወይም ተቋም ውክልና መስጠት ይችላል፤

፳/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የአሰራር ደንብ እና የአሰራር ሥርዓት ሊቀርፅ ይችላል።

## ፲፫. የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠያቂነት

፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን በተገቢው ጥንቃቄ መወጣት አለባቸው።

፪/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የቦርድ አባልነት ስራቸው አጋጣሚ ያገኙዋቸውን ሚስጥራዊ መረጃዎች የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።

14/ Set the dividend policy of Ethiopian Investment Holdings and its subsidiaries balancing the sustainable distribution of profits as dividends to the government including resources needed for national investment, debt servicing, budget and other policy objectives with that of the retention of profits for Ethiopian Investment Holdings investment to generate future returns;

15/ Approve external Auditor report of the Ethiopian Investment Holdings and follow up that corrective measures are taken as per the audit findings;

16/ Approve Memorandum of the Ethiopian Investment Holdings as may be necessary;

17/ Decide on remuneration and other benefits of Board of Directors;

18/ Perform other functions that may be prescribed in Ethiopian Investment Holdings' internal rules and regulations as well as other mandates that may be necessary for the protection of the ownership rights of the government in the Ethiopian Investment Holdings and its subsidiaries;

19/ The Board may delegate to any person, a committee or institution the exercise of any powers or the performance of any of its functions or its duties under this Regulation;

20/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may draw up its own rules of procedure.

## 13. Liability of the Board of Directors

1/ The Board of Directors shall carry out their duties with due care.

2/ Members of the Board shall be committed to maintain confidentiality of the information made available to them while exercising membership tasks thereof in the Ethiopian Investment Holdings.

https://chilot.me


፫/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የመልካም ሥነ-ምግባር ደንብ እና መመሪያ ማክበር አለባቸው።

3/ Members of the Board shall observe Ethiopian Investment Holdings' code of good practice and guidelines.

## ፲፬. የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣን እና ተግባር

ዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚከተለው ሥልጣን እና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩/ በዚህ ደንብ በተቀመጡት ዓላማዎች እና በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ስትራቴጂክ ራዕይ እና አጠቃላይ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ይቀርፃል፤

፪/ በዚህ ደንብ እና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሰትራቴጂያዊ ዓላማዎች መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የእለት ተለት ስራዎች ይመራል፤

፫/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን የውስጥ ደንቦች እና በጀት እንዲሁም የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚከስበትንም ሆነ የሚከሰስበትን ጉዳይ ጨምሮ ከሶሰተኛ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት ይወክለዋል፡፡ ይህንኑ በተመለከተም ድርጅቱን የሚወክል እንደራሴ ወይም የሕግ ባለሙያ ይወክላል፤

፭/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በተቋቋመለት ዓላማ ውስጥ የሚወድቁ ውሎችን፣ ስምምነቶችን እና ግብይቶችን በሙሉ ያደርጋል፤

፮/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል

፯/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስን ሰራተኞችን ደመወዝ፣ ቦነስ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን በማስጠናት በቦርዱ ያስወስናል፤ ስራ ላይ ያውላል፤

፰/ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የባንክ ሒሳቦች ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ይዘጋል፤

## 14. Powers and Responsibilities of the CEO

The CEO shall have the powers and responsibilities to:

1/ Develop the strategic vision and the general investment policy of Ethiopian Investment Holdings in line with the objectives set out under this Regulation and directions of the Board of Directors;

2/ Manage the day-to-day operations of Ethiopian Investment Holdings in accordance with this Regulation and its strategic objectives;

3/ Prepare and submit to the Board the internal regulations as well as the work program and budget of Ethiopian Investment Holdings and implement same upon approval;

4/ Represent the Ethiopian Investment Holdings in respect of its relations with third parties including legal proceedings brought by or against it or delegate agents and legal representatives to act on its behalf;

5/ Conclude all contracts, agreement and transactions falling within the objectives of Ethiopian Investment Holdings;

6/ Hire, suspend and remove the staff of Ethiopian Investment Holdings;

7/ cause to Study and submit to the Board's approval the salaries, bonus and other remunerations of the staff of Ethiopian Investment Holdings; and implement same;

8/ Open, operate, and close bank accounts for the Ethiopian Investment Holdings;

https://chilot.me


፱/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሒሳብ ሰነዶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃዎች እና በሌላ በማናቸውም የሃገሪቱ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

9/ Ensure proper books of accounts of the Ethiopian Investment Holdings are maintained in accordance with internationally accepted accounting standards and any other national rules and regulations;

፲/ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፤

10/ Submit performance reports to the Board of Directors;

፲፩/ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተሰጡትን ሌሎች ኃላፊነቶች ወይም ተግባራትን ያከናውናል።

11/ Perform other duties assigned to him/her by the internal regulation of Ethiopian Investment Holdings.

## ፲፭. ተጠያቂነት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

## 15. Liability

The Ethiopian Investment Holdings shall not be liable beyond its total assets.

## ፲፮. ከግብር ነፃ ስለመሆን

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በባለቤትነት ከያዛቸው ድርጅቶች የሚያገኘው የትርፍ ድርሻ ከማናቸውም ግብር፣ ቀረጥና ተመሳሳይ የክፍያ ግዴታ ነፃ ነው።

፪/ ይህ የግብር ነፃ መብት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ላቋቋማቸው ንዑስ ፈንዶች እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ባለአክሲዮን ለሆነባቸው ኩባንያዎች ተፈፃሚ አይሆንም።

፫/ ይህ ተፈጻሚ የሚደረገው በሌላ ሕግ የተደነገጉ ማንኛውም ከግብር ነጻ የሚያደርጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ነው።

## 16. Tax Emption

1/ Dividends of the Ethiopian Investment Holdings from its organizations shall be exempted from all taxes, duties and the like.

2/ Such exemptions shall not apply to the sub-funds and companies in which Ethiopian Investment Holdings is a shareholder.

3/ This shall take place without prejudice to any exemptions stipulated in other law.

## ፲፯. የሂሳብ ዓመት

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሂሳብ ዓመት የኢትዮጵያ መንግስት የበጀት ዓመት ሲሆን ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ፴ ቀን የሚቆጠር ይሆናል።

፪/ በተለያዩ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) የተገለጸውን የሂሳብ ዓመት መከተል የማይችል ከሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድን በማስፈቀድ የተለየ የሂሳብ ዓመት ለመጠቀም ይችላል።

## 17. Financial Year

1/ The financial year of Ethiopian Investment Holdings shall be the Ethiopian government fiscal year that begins on Hamle 1st and ends on Sene 30th of the Ethiopian calendar.

2/ However, if Ethiopian Investment Holdings is unable to use the financial year prescribed under Sub-Article (1) above for various reasons, it may use a different financial year with the permission of the Board of Directors.

https://chilot.me


## ፲፰. ኦዲት

፩/ የፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እሱ የሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሂሳቦች በውስጥ ኦዲተር እና ቦርዱ በሚሾመው ገለልተኛ የውጭ ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

፪/ ኦዲተሮቹ የሩብ ዓመትና የዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎችን ይመረምራሉ፡፡

፫/ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎች፣ የኦዲተር ሪፖርት፣ እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዝርዝር የዓመቱ ሪፖርት እንዲሁም ለሚቀጥለው ዓመት የሚያዘጋጀው ዕቅድ የዓመቱ የሂሳብ ዘመን ባለቀ በሦስት ወር ውስጥ ለቦርድ መቅረብ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ስር ያለ ሀብት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ደረጃዎች መሠረት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሒሳብ መዝገብ ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

## ፲፱. ቆይታ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ላልተወሰነ የቆይታ ዘመን የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

## ፳. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፶፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና ተቆጣጣሪ ኤጄንሲን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፬፻፵፭/፪ሺ፲፩ እና ሌላ ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## 18. Audit

1/ Without prejudice to the powers and duties of the Federal Auditor General or its designee Auditor under other laws, the accounts of Ethiopian Investment Holdings shall be audited by both internal and external independent Auditor to be assigned by the Board.

2/ The Auditors shall audit the annual and quarterly financial statements.

3/ The annual financial statements, the Auditor's report and the detailed annual report about the activity of Ethiopian Investment Holdings and its plan for the next year shall be submitted to the Board of Directors, within three months from the end of each financial year.

4/ Any asset under the Ethiopian Investment Holdings shall be recorded in its ledger in accordance with internationally accepted accounting standards.

## 19. Duration

The Ethiopian Investment Holdings is established for an indefinite duration.

## 20. Inapplicable Laws

Without prejudice to Article 54 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021, the Definition of Powers and Duties of the Public Enterprises Holding and Administration Agency Regulation No. 445/2019 and any other law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Regulation, have no force or effect in respect of matters provided for by this Regulation.

https://chilot.me


**፳፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.**

**ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**21. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa on this 31st day of January, 2022.**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**